በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማ እና ትንበያ መጽሔት

## ከኤፕሪል 21-30/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ እንዲሁም

## ከሜይ 1-10 እና ከሜይ 11-20/2024

## የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ሜይ 2024

አዲስ አበባ

ስልክ +251115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

**ርዕስ** **ገፅ**

**እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21 እስከ 30/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ** - 1 -

ምስል 1 የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ - 2 -

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ - 3 -

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21 እስከ 30/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት - 3 -

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር - 3 -

እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21 እስከ 30/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ - 4 -

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ - 4 -

እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21 እስከ 30/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ - 5 -

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ - 5 -

እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ - 6 -

ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከሜይ 1-10, 2024 - 7 -

የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ - 7 -

ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከሜይ 1-10, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ - 7 -

እ.ኤ.አ ከይ 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ - 7 -

ካርታ 8 እ.ኤ.አ ከሜይ 11-20፣ 2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ - 8 -

እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ - 8 -

እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ - 9 -



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21 እስከ 30/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ

ባለፉት ቀናት በሰሜን ምስራቅ፣ በመካከለኛዉ፣ በምስራቅ፣ በደቡብ፤ በደቡብ ምዕራብ እና በደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ጠንካራ የደመና ሽፋን እና ክምችት ነበራቸው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በልግ ዋነኛና ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብ እና ደቡብ ምዕራብ እንዲሁም መካከለኛው፣ ምስራቅ፣ ሰሜን ምስራቅ፣ ደቡብ ምስራቅ እና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል በአዲስ አበባ ቦሌ 34.8፤ አዲስ አበባ ጥቁር አንበሳ 81.4፤ በአርባ ምንጭ 41.8 እና 42.7፤ አልጌ 45.0፤ በጎዴ 30.5፤ በአማን 35.2፤ በቦሬ 30.4፤ በቡኢ 45.4፤ በቡሌ ሆራ 42.9፣ 72.8፤ በዳሊፋጊ 35.3 እና 48.2፤ በዲላ 39.8፤ በዶሎመና 30.2፣ 40.2 እና 30.0፤ በዲላ 39.8፤ በጊኒር 52.0፤ በቡሌሆራ 42.9 እና 73.8፤ በእምድብር 34.2 እና 43.1፤ በኮንሶ 32.5 እና 32.0፤ በማጀቴ 33.0፤ በማጂ 42.7፤ በሞያሌ 45.2 እና 76.0፤ በሚሌ 54.0፤ በነጆ 31.2፤ በሳዉላ 37.9፤ በሰመራ 30.0፤ በሲሪንቃ 39.0፤ በያቤሎ 40.4፤ በኮምቦልቻ(ምስራቅ ሀረርጌ) 48.2፤ በካራሚሌ 38.5፣ በጨለንቆ 30.0 እና 42.4፤ በአዋሬ 31.0፤ በዶሎ 30.4፤ በሀራዋ 34.6፤ በሽላቦ 61.0፣47.5 እና 114.5፤ በጉብዬሬ 49.8፤ እንዲሁም በአለም ተፈሪ 44.2 በሚ.ሜ ይገኙበታል።


ባለፉት ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ፣ ቦረና እና ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ እና ደቡብ ምዕራብ ሸዋ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ ቄለም ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ እና ኢሉባቦር ዞኖች፤ ሁሉም የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል፤ የደቡብ እትዮጵያ ክልል፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል እና የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ካማሺ ዞን፤ ከሱማሌ ክልል ሲቲ፣ ፋፋን፣ ኤርር፣ ዶሎ፣ጀረር ቀራሄ፣ ዶሎ፣ ኖጎብ፣ ሸበሌ፣ አፍዴር፣ ሊበን እና ዳዋ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ሰሜን ወሎ እና የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፤ ከአፋር ክልል ሀሪ፣ ሀዉሲ እና ጋቢ ዞኖች ላይ ከ31-160 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ7-10 ቀናት ያህል ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን፣ ከትግራይ ክልል ምስራቅ፣ ማዕከላዊ፤ሰሜን ምዕራብ፣ ደቡብ ምስራቅ እና ምዕራብ ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል



ስልክ +251115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

መተከል፣ የማኦኮሞ ልዩ ዞን እና አሶሳ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ቂልበቲ እና ፋንቲ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ሰሜን፣ ማዕከላዊ፣ ደቡብ እና ምዕራብ ጎንደር፣ ደቡብ ወሎ፣ ዋህግምራ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ ሰሜን ሸዋ አዊ ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ክልል አርሲ፣ምዕራብ ሀረርጌ፣ ሰሜን ሸዋ(ሰላሌ) እና ምዕራብ ወለጋ ዞኖች ላይ ከ5-31 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ1-5 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ።


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ጉጂ እና ምዕራብ ምዕራብ ጉጂ፣ቦረና እና ምስራቅ ቦረና፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ቀለም ወለጋ፣ ሁሉም የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል፣ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል እና የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከሱማሌ ክልል ሲቲ፣ፋፋን፣ ኤረር፣ ኖጎብ፣ ጀረር፣ዶሎ፣ ቆራሄ፣ ሸበሌ፣ አፍዴር፣ ሊበን እና ዳዋ ዞኖች፤ ሁሉም የአፋር ክልል ዞኖች፤ ከትግራይ ክልል ምስራቅ፣ የደቡብ ምስራቅ፣ ማዕከላዊ እና ምዕራብ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ሰሜን፣ ማዕከላዊ፣ ደቡብ እና ምዕራብ ጎንዳር፣ ዋህግምራ፣ ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ ሰሜን ሸዋ፣ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም ዞኖች፤ አዲስ አበባ፣ ድሬ ዳዋ እና ሀረር ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን አግኝተዋል (ካርታ 3) ።





ምስል 1 የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ




ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21 እስከ 30/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር




ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21 እስከ 30/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት አስር ቀናት የበልግ አብቃይና ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተገኘው እርጥበት ቀደም ብለው ለተዘሩና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የበልግ ሰብሎች፣ ለጓሮ አትክልቶችና ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ በተጨማሪም የነበረው እርጥበት ቀደም ብለው በኤፕሪል መጨረሻ ወር ላይ ለሚዘሩ የመኸር ወቅት ሰብሎች ማሳን ለማዘጋጀትም ሆነ ዘር ለመዝራት ምቹ እንደነበረ የተተነተኑ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪም የተገኘው እርጥበት በአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለመጠጥ ውሃና ለግጦሽ ሣር አቅርቦት መሻሻል የጎላ ጠቀሜታ ነበረዉ፡፡

በሌላ በኩል በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ የነበረው ከፍተኛ መጠን ያለው እርጥበት በረባዳማ እና የአፈር ጸባያቸው ውሃን በማያሰርጉ ማሳዎች እንዲሁም በወንዝ ዳርቻ አካባቢዎች በሚገኙ ማሳዎች ላይ መጠነኛ የሆነ የውሃ በሰብሎች ላይ መተኛት እና በደለል የመሞላት እንዲሁም በጎርፍ የመጠረግ ሁኔታዎች ተስተውሏል (ካርታ 4) ፡፡





ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21 እስከ 30/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት አስር ቀናት በኦሞጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ገናሌዳዋ፣ ዋቤ ሸበሌ፣ አፋር ደናክል፣ ኦጋዴን፣ በላይኛውና በመካከለኛው አዋሽ፣ በጥቂት የላይኛውና የመካከለኛው አባይ፣ ባሮ አኮቦ፣ እንዲሁም በላይኛው ተከዜ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የእርጥበት ሁኔታ እንደነበራቸው የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ። ይህም ሁኔታ የገጸ ምድርንም ሆነ የከርሰ ምድር የውሃ ሀብትን በማጎልበት ወደ ተለያዩ የውሃ መያዣዎች እና ማጠራቀሚያዎች የሚገባውን የውሃ ሀብት ከመጨመር አንጻር ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው። በሌላ በኩል የተቀሩት በአብዛኛው ተከዜ፣ የታችኛው አባይ፣ ባሮ አኮቦ፣ የታችኛው አዋሽ እና በጥቂት የመካከለኛው ዋቤ ሸበሌ ተፋሰሶች ደረቅ እና ከፊል ደረቅ የአየር ሁኔታ ላይ ነበሩ (ካርታ 5)።




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ


በሜይ የመጀመሪያዎቹ አስር ቀናት ለዝናብ መፈጠር አስዋጽኦ የሚያደርጉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ። በመሆኑም በሚቀጥሉት አሥር ቀናት የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ ስፍራዎች ላይ ለዝናብ መፈጠር አመቺ የሆኑ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች አንጻራዊ ጥንካሬ እንደሚኖራቸውና በተለይም የምድር ወገብን በማቋረጥ ወደ ሀገራችን የሚገባው ዕርጥበት አዘል የአየር ሁኔታ ጋር ተያይዞ የተሻለ የደመናና የዝናብ ሥርጭት ይኖራቸዋል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በደቡብ፤ በደቡብ ምስራቅ፣ በሰሜን ምስራቅ፣ በምስራቅ፣ በመካከለኛዉ፣ እንዲሁም በስምጥ ሸለቆ አካባቢዎች የተሻለ የዝናብ መጠንና ስርጭት ይኖራቸዋል (ካርታ 6 እና 7 )፡፡ በመሆኑም በበልግ አብቃይ አከባቢዎች በርካታ ቦታዎቻቸውን የሚሸፍን ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 7)፡፡ በተጨማሪም በውሃ አካላትና በከባቢ አየር ውስጥ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በደቡብ፣ በደቡብ ምስራቅ፣ መካከለኛው፤ በምስራቅና በሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ቅጽበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል የሚችል ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 6 እና 7)፡፡

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት ቀናት ከኦሮሚያ ክልል ጅማ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ አርሲና ምዕራብ አርሲ፣ ባሌና ምስራቅ ባሌ፣ ጉጂና ምዕራብ ጉጂ፤ ቦረና፤ ምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ፣ እንዲሁም ሐረሪ እና ድሬዳዋ፤ አዲስ አበባ፤ ከአማራ ክልል የሰሜንና የደቡብ ወሎ ዞኖች፣ የዋግህምራ፣ የሰሜን ሸዋና የኦሮሚያ ልዩ ዞን፣ የአፋር ክልል ዞኖች፤ ከትግራይ ክልል የደቡብ፣ የደቡብ ምስራቅ፣ ማዕከላዊ፤ የምስራቅ ትግራይ ክልል ዞኖች፤ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ የሱማሌ ክልል ዞኖች የተስፋፋ ዝናብ የሚኖራቸው ሲሆን፤ በአንዳንድ ስፍራዎቻቸው ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6)፡፡ በተጨማሪም ከኦሮሚያ ክልል ቄለም ወለጋ፣ ሁሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፤ ከአማራ ክልል የደቡብ ጎንደር ዞን፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የምስራቅና የምዕራብ ጎጃም ዞኖች፤ የጋምቤላ ክልል ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ክልል የአሶሳ፣ የማኦኮሞ ልዩ ወረዳ፤ ከቀላል እስከ




ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 7)። በተጨማሪም በአፋር ክልል፤ ሀረር፤ ድሬዳዎ፤ የሶማሌ ክልል ዞኖች፤ አዲስ አበባ፣ በደቡብ ኢትዮጵያ እና በምስራቅ አማራ አከባቢዎች ከሚኖረው ተደጋጋሚነት ያለው ከባድ መጠን ያለው ዝናብ በመነሳት ቅጽበታዊ ጎርፍ የማስከተል አቅም ስለሚኖረው ከወዲሁ ማህበረሰቡና የሚመለከታቸው አካላት አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚያስፈል የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ይጠቁማል (ካርታ 6)።




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከሜይ 1-10, 2024

የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከሜይ 1-10, 2024

የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ


## እ.ኤ.አ ከይ 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በሜይ ሁለተኛዉ አስር ቀናት ለዝናብ መፈጠር አስዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለይም በደቡብ አጋማሽ ላይ ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከዚህ ጋር ተያይዞ በሚቀጥሉት አሥር ቀናት የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ ስፍራዎች ላይ ለዝናብ መፈጠር አመቺ የሆኑ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ጥንካሬ እንደሚኖራቸውና በተለይም በልግ ዋናኛና ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በደቡብ፣ በምስራቅ፣ በሰሜን ምስራቅ እና በመካከለኛው የሀገራችን አከባቢዎች ላይ ከቀላል



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸዉ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 8) ።




ካርታ 8 እ.ኤ.አ ከሜይ 11-20፣ 2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

## እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት ቀናት የሚጠበቀው እርጥበት ቀደም ብለው ለተዘሩ በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የበልግ ሰብሎች፣ ለጓሮ አትክልቶችና ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከሜይ መጀመሪያ ጀምሮ ለሚዘሩ የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎች አዎንታዊ ሚና የሚኖረው ሲሆን፤ ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የእፅዋት ልምላሜ፣ የግጦሽ ሳር እና የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ከማሻሻል አንጻር የሚኖረው ፋይዳ ከፍተኛ ነው፡፡

በሌላ በኩል ውሃ ገብ በሆኑና በወንዝ ዳርቻ ባሉ ሰብሎች ላይ የውሃ መተኛት፣ የአፈር መታጠብን እንዲሁም የመሬት መንሸራተት ሊያስከትል ስለሚችል ለዚሁ ችግር



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ተጋላጭ የሆኑ አካባቢዎች ጉዳትን ለመቀነስና ብሎም ለማስቀረት የሚያስችሉ የውሃ ማንጣፊፍያ እና የጎርፍ መቀልበሻ ቦዮችን ከወዲሁ በማዘጋጀት ጥቅም ላይ ማዋል ያስፈለጋል።

## እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የሜይ የመጀመርያው አስር ቀናት በገናሌ ዳዋ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ አዋሽ፣ ዋቤ ሸበሌ፣ አፋር ደናክል የላይኛው እና መካከለኛው አባይ፣ ተከዜ እና በላይኛው ባሮአኮቦ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ እርጥበት ይኖራቸዋል፡፡ ይህም ሁኔታ የገፀ ምድር እና የከረሰ ምድር ውሃ ሀብትን ከማጎልበት አንጻር አዎንታዊ ሚና  የሚኖረው ሲሆን፤ በተጨማሪም ለመስኖም ሆነ ለሀይል ማመንጫነት የሚያገለግሉ ግድቦች ከመደበኛ በላይ የሆነ የውሀ መጠን ይዘው እንዲቆዩ ከማሰቻል አንንጻር አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል።

በአንጻሩ ግን  በአንዳንድ ተፋሰሶች ላይ የሚጠበቀው ከፍተኛ መጠን ያለው እርጥበት በተለይም ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ  የከተማም ሆነ የገጠር አካባቢዎች ላይ በንብረትና በሰው ህይወት ላይ ጉዳት ሊያስከትል ስለሚችል አደጋን ለመቀነስ ብሎም ለማሰቀረት የሚያስችሉ መደበኛ የውሃ መፋሰሻዎችን የማጽዳት፣ የጎርፍ መቀለበሻ ቦዮችን የማዘጋጀት እና  ለጎርፍ ተጋላጭ የሆኑ የወንዝ ዳርቻዎችን የመገደብ ተግባራትን አስቀድሞ ማከናወን ያስፈልጋል፡፡



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et